# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## አቤቱ ዓይኖቻችንን ክፈት

የባልንጀራን መውደድ ጉዳይ ከብዙ አንጻር ሊተነተን ይችላል። ከብዙ አንጻር ሊነሳ የሚችል ጉዳይን፣ ስለምን ከመጽሐፍ ቅዱሳችን አንጻር ልንመለከተው መረጥን? ምክንያታችን ግልጽ ነው፤ ባልንጀራን መውደድ የመጽሐፍ ቅዱስ አንኳር መልእክት ስለሆነ! ይህ ብቻ አይደለም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ያካተታቸው መጽሐፍት ሁሉ ለእኛ ለክርስቲያኖች ቅዱሳት ከመሆናቸው የተነሳ ነው።

አንደ ክርስቲያን ለመጽሐፍ ቅዱስ ከፍ ያለ ስፍራን የሰጠነው እኛነታችንን ለመቅረጽ የታመነ ሆኖ ስላገኘነው ነው። ስለዚህም ለሥልጣኑ ራሳችን በማስገዛት መንፈስ ቅዱስ የሚናገረንን ለመስማት ራሳችንን እናዘጋጃለን። ቅዱስ ቃሉ ለሕይወታችን የተሰጠ መመሪያ እንደ ሆነ በማመንም፣ እግዚአብሔር ከሕይወታችን፣ ከአስተሳሳሰባችንና ከድርጊታችን የሚጠብቅብን ነገር ምን እንደሆነ ከቅዱስ ቃሉ እንማራለን።

ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ማንነታችንን በመቅረጽ ሂደት ሙሉ ሥልጣን አለው የሚለው እምነታችን፣ አምላካችን በቅዱስ ቃሉ የገለጠውን ፈቃዱን ለማወቅ፣ ቅዱሳት መጽሐፍትን በትጋትና በጥንቃቄ እንድንመረምር ግድ ይለናል። ከዚህም የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ አምላካዊ መልእክት መሆኑን በመገንዘብ፣ እግዚአብሔርን ሊሰማ እንደፈለገ ሰው በትህትና፣ በአክብሮት እንዲሁም በጸሎት ሆነን እንቀርበዋለን።

በጸሎት የተሞላ ንባብ (prayerful reading)፣ ወደ አሰላስሎ (meditation and contemplation) እና ወደ ድርጊት (action) ይመራናልና። ይህ ካልሆነና ራሳችንን በታዛዥ ልብ በእግዚአብሔር ፊት ካላቀረብን፣ የቃሉ ሰሚዎች እንጂ አድራጊዎች ልንሆን ከቶ አይቻለንም።

የቃሉን በጸሎት ስንቀርብ፣ መረዳትን እና ምሪትን ለሚሰጥ ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን ማስገዛት እንለምዳለን። ቅዱስ ቃሉ ሀሳባችንን ሲገዛ፣ እንደ ቃሉም መጸለይ ስንጀምር፣ እግዚአብሔርን ደስ እናሰኛለን። ልክ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን ደስ ከማሰኘት የሚበልጥ ሌላ ናፍቆትም ሆነ ቅንዓት የለንም (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡9)።

የቃሉ ባለቤት መንፈስ ቅዱስ መረዳት እንዲሰጠን ስንጠይቅ፣ ዓይኖቻችን ይከፈታሉ፣ በቃሉ እና በመንፈሱ አማካኝነት በምን መልኩ መለወጥ እንዳለብን እንረዳለን፤ የሚያስፈልገንንም ጸጋ እንዲሁ እንቀበላለን።

ቃሉ ጽኑእ ነው፣ እንድንበታለንም (ማርቆስ 13፡31፤ ያዕቆብ 1፡21)። ንጉስ ዳዊት ይህንኑ እውነታ በመረዳት፣ "ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ" ብሏል (መዝ 119፡18)። የእኛም ጸሎት ይህ ነው።

አቤቱ ባልንጀራን መውደድን እንድንረዳ ዓይኖቻችንን ክፈት፣ የተረዳነውንም እንድንኖረው ቅዱሱ መንፈስህ ጸጋን ያብዛልን!

## የዘነጋነው ዋና ነገር

አራቱ ወንጌላት የጌታን ሕይወትና ትምህርቶች ይተርካሉ። ከአራቱ በሶስቱ ተመሳሳይ ወንጌላት እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን መውደድ የክርስቶስ ዋነኛ ትእዛዛት ሆነው ቀርበዋል (ማርቆስ 12፡28-34፤ ማቴዎስ 22፡34-40፤ ሉቃስ 10፡25-37)።[1] ትእዛዛቱ በወንጌላቱ መደጋገማቸው ያለምክንያት አይደለም፤ ባልንጀራን መውደድ ላቅ ያለ ስፍራ ስለተሰጠው እንጂ። ይህንኑ እውነታ ስኮት ጄ ጆንስ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡-

> የሶስቱን ወንጌላት የባልንጀራን መውደድ መልእክቶች በጥምረት ስንመለከታቸው፣ እግዚአብሔርን በሁሉ ነገራችን መውደድና ባልንጀራችንን እንደ ራሳችን መውደድ፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ዋንኛ፣ ማዕከላዊ፣ እና ከሁሉ የላቀ ትዕዛዝ መሆኑን እንገነዘባለን። ሌሎች ኃላፊነቶች ሁሉ የሚገዙት ለእነዚህ ሁለት ትዕዛዛት ነው።[2]

ከስኮት ጆንስ ገለጻ ሁለት ነገሮች ላይ እናተኩር። የመጀመሪያው፡- የጌታችን የባልንጀራን መውደድ ትምህርት እግዚአብሔር ከሁሉም ሰዎች የሚጠብቀው ነገር መሆኑን ነው። ባልንጀራን መውደድ ለእያንዳንዳችን የታየልን ቅዱሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ፈቃዱን ለማወቅና ለመኖር ራሱን እንደሚያዘጋጅ የክርስቶስ ተከታይ፣ ባልንጀራን መውደድ የምንሸሸው ሸክም አይደለም! ይህንን ትዕዛዝ የማንሸሸው ጌታ የእርሱ ቀንበር ልዝብ፣ ሸክሙም ቀሊል መሆኑን ስለነገረንም ነው (ማቴዎስ 11፡

1 ተመሳሳይ ወንጌላት ተብለው የሚታወቁት የማቴዎስ፣ የሉቃስና የማርቆስ ወንጌላት ናቸው።

2 Scott J. Jones, *The Evangelistic Love of God and Neighbor: A Theology of Witness and Discipleship* (Nashville, TN: Abingdon Press, 2003), 51.

30)። ባልንጀራችንን ሳንወድ፣ ክርስቶስን የምንወድበት ሆነ የክርስቶስ እውነተኛ ደቀ መዝሙሮች የምንሆንበት አቋራጭም አማራጭም የለም!

የጌታችን የባልንጀራን የመውደድ ትምህርት እጅግ ያስገርማል። ሰውን ሁሉ ያለ አንዳች ልዩነት እንድንወድ ይጠብቃል (ማቴዎስ 5፡38-42)! ለሚደርስብን በደልና ጥቃት አጸፋ ከመስጠት ይልቅ የበለጠ ፍቅርን በማሳየት በጥላቻና በበቀል እንዳንሸነፍ ያዛል (ማቴዎስ 5፡38-42)! የሚወዱንንና መልካም የሆኑልንን ብቻ ሳይሆን፣ የሚጠሉንንም ከኛ ወገን ያልሆኑትንም ጭምር እንዳንሸሽ፣ ይልቁንም እንደ ራሳችን እንድንወዳቸው ያስተምራል! እነዚህ መርሆች በዓለም መስፈርት በርግጥም ሞኝነት ናቸው! አስገራሚው የጌታ ትምህርት ግን የሁሉ አዋቂው የእግዚአብሔር ጥልቅ እውነታዎችና ለልጆቹ በቸርነቱ የገለጣቸው የጥበብ መንገዶች እንደሆኑ ያሳየናል።

ጌታ ባልንጀራን መውደድን ሰብኳል፤ ሕይወቱም ያንኑ አሳይቷል። ሰው የሚጠየፋቸውን መንካት አልከበደውም (ሉቃስ 5፡12-16)፤ የተራቡትን አጥግቧል (ሉቃስ 9፡10-17)፤ ባሮችን ፈውሷል (ሉቃስ 7፡1-10)፣ ከሚጠሉት ጋር ማዕድ ተቋድሷል (ማርቆስ 2፡15-17)፤ በኃጢአት እጅ ከፍንጅ ለተያዙ ምህረት አድርጓል (ዮሐንስ 8፡3-11)፤ ሲሰቅሉት ጸሎቱ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ነበር (ሉቃስ 23፡34)። በእኒህ ሁሉ፣ ፍቅሩ ማንንም እንደማያገል፣ ለሁሉ እንደሚራራና ምህረት እንደሚያደርግ ታይቷል።

ጌታችን ሚዛኑ ከዘመኑ ይለይ ነበር። ለምጽን እንደምሳሌ እናንሳ። በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የለምጽ በሽታ እጅግ ይፈራ ነበር፤ ለምጽ መድሀኒት የለውም፣ ይተላለፋልም ተብሎ ስለሚታመን ለምጽ የያዘውን ሰው መሸሽ የተለመደ ነበር። በዚሁ ስሌት፣ ሕጉ በመቅደስ የሚያገለግሉ ካህናቱ ለምጻሙን ከቤቱና ከከተማው እንዲያበሩት ይፈቅድላቸዋል (ዘሌዋውያን 13-14)።

በለምጽ መያዝ መዘዙ ብዙ ነው፤ ከማኅበራዊና ከሃይማኖታዊ ትስስሮች ያርቃል። በጌታ ዘመን ለምጻሞች ቅጥር ካላቸው ከተሞች ሁሉ ይባረራሉ። ሰውን በማርከስም ለምጻምን መንካት በድንን ከመንካት ቀጥሎ ሁለተኛው ነበር። ለአምልኮት በምኩራብ አይሁዶች ሲሰበሰቡም የለምጻሞች ፈንታ በጠባብ ክፍል ተለይቶ መቀመጥ ነበር።[3] ቸሩ ጌታ ይህን ሁሉ ገደብ አልፎ በርህራሄ ለምጻሞቹን ነክቷቸዋል (ማቴዎስ 8፡1-4)።

መነካትን እንዳናቀለው፤ ለለምጻሞች መነካት ብርቃቸው ነው! ለረጅም ዘመን ተነክታችሁ ባታውቁና አንድ ሰው ሲነካችሁ የሚሰማችሁን አስቡት። የነካችሁ ሰው እንዳከበራችሁና እንደወደዳችሁ ፈጽሞ አይጠፋችሁም። ዝም በሉ ብትባሉም

3 William Barclay, *The Gospel of Matthew* (Louisville, KY: Westminster John Knox Press, 1968), 340-342.

አትችሉም፣ ደስታ ፈንቅሎ ያናግራችኋል። በጌታ ንኪትም የሆነው ይህ ነው (ማርቆስ 1፡ 45)።

ስኮት ጆንስ ያሰመረበት ሁለተኛው ነገር ባልንጀራን መውደድ ሌሎች ትምህርቶች ሁሉ የሚፈልቁበት ምንጭ መሆኑን ነው። ባልንጀራን ከመውደድ ያልመነጩ በጎነቶች የሆነ ዓይነት ስንኩልነት አለባቸው። የዚህ ምክንያት ደግሞ ከፍቅር መጉደል፣ ከምልዐት መጉደል ስለሆነ ነው።

የጌታ የባልንጀራ የመውደድ ትምህርት፣ ለሁሉ የተዘረጋ እጅ ነው። ጆን ዌስሊም ይህንኑ ተገንዝቦ "ባልንጀራን መውደድ ለሰው ሁሉ የሆነ ቸርነትና በጎነት የሚንጸባረቅበት ርሁሩሁነት ነው። የሰው ልጅ የሆነ ሁሉ፣ የአዳም ልጅ ሁሉ፣ ባልንጀራችን ነው። የጌታችን የደጉ ሳምራዊ ታሪክም የሚያስተምረን ይህንኑ ነው።"[4] ብሏል። ሰው ሁሉ ባልንጀራችን ነው፤ ፍቅራችንም ይገባዋል የሚለው ሃሳብ የወንጌላችን መልእክት ነው።

ባልንጀራችን አንዳንዶቻችን እንደምናስበው ጎረቤታችን ብቻ አይደለም፤ ሁሉ ባልንጀራችን ነው። የተወደድንበት አምላካዊ ፍቅር ማንንም እንደማይገፋ ሁሉ፣ ፍቅር ሊነፈግ የተገባው ማንም የለም። ፍቅር በኃጢአት ያዝናል እንጂ ኃጢያተኛን አይገፋም። ጌታ እኛን በወደደን መንገድ፣ እኛም ፈለጉን ተከትለን አንዱን ከሌላው ሳንለይ እንድንወድ ተጠርተናል።

ጌታችን እንድንሳተፍበት የጋበዘን ፍቅር ያሻውን የሚያነሳና የማይፈልገውን የሚተው አይደለም። ፍቅሩ በሰው ልጆች ላይ ሳይለይ የሚወጣውን ፀሀይና የሚዘንበውን ዝናብ ይመስላል። ፀሀይና ዝናብ መራጮች አይደሉም! ልክ እንደ ፀሀይና ዝናብ ከክርስቶስ የተካፈልነው ፍቅር ያገኘናቸው ሁሉ ፍቅራችን የተገባቸው አድርጎ ይቆጥራል። ሰው ሁሉ በፊታችን፣ አንዳች ምላሽን ለመቀበል ሳናስብ የምናስተናግደው የፍቅ እንግዳችን ነው።

የተወደድንበት (ኤፌሶን 3፡17-19) እና እግዚአብሔር እንድንወድበት በልባችን ያፈሰሰው ፍቅሩ (ሮሜ 5፡5) ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቀቱም ከሰው ማስተዋል ያልፋል። በዚህ ፍቅር የማይዋጥ ማንነት የለም! ስለዚህም፣ በዚሁ በተጠመድንበት ፍቅሩ፣ እርሱን ደስ ልናሰኝና በበጎ ሥራ ፍሬን ልናፈራ እናድጋለን (ፊሊጲሲዮስ 1፡9-11)።

የፍቅር ውሎ ክስ ማስነሳቱ አይቀርም። ጌታም እኮ የኃጢያተኞች ወዳጅ ተብሏል (ማቴዎስ 9፡11፣ 11፡16-19)። እንደ ችግር የተቆጠረበት ማዕድ አብሮ መታደሙ ነበር (ሉቃስ 19፡5-7)፣ ሁሉን መውደዱ ጌታን አስተችቶታል። የተቹት ተልዕኮውን አልተረዱም፤ የእርሱ ጥሪ እኮ ኃጢያተኞችን ማዳን ነው (1ኛ ጢሞቲዎስ 1፡15፤ ሉቃስ 5፡32)። እኛም ዛሬም፣ ኃጢያተኞችን በመወዳጀታችን ከተከሰስን፣ ጌታችን በታማበት ስለ መታማታችን ክብር ይሰማናል።

4 John Emory and John Wesley, *The Works of the Reverend John Wesley*, AM Volume (Electronic Resource, 1831), 814.

የሳምራዊቷን ታሪክ እናስብ (ዮሐንስ 4፡1-42)። ሴት መሆኗ፣ ከሳምራውያን መገኘቷ፣ በታሪኳ ብዙ ባሎች የነበራት ብቻ ሳትሆን አሁንም ባሏ ካልሆነ ሰው ጋር አብራ እየኖረች መሆኗ፣ በፍቅር ርህራሄ እንዳያናግራት ለጌታ መደናቀፍ አልሆነውም። የጌታ ፍቅር በእውነት ይጋፈጣል እንጂ ለማራቅ አይገፋም። የእኛም ፍቅር እንደ እርሱ ጾታ፣ ቀለም፣ ዘር፣ ጎሳ፣ ማኅበራዊ ደረጃና ሌሎች ለእኛ ባላቸው ስሜት ላይ ሳይመሠረት ሁሉን ማቀፍ አለበት።

ጌታችን እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን መውደድን ከሕግጋት ሁሉ አስበልጧቸዋል። ግን ለምን? ሕግጋቱ የትዕዛዛት ሁሉ መጠቅለያ ስለሆኑ። ሙሴ እስራኤል እንዲገዛባቸው የተቀበላቸው አስርቱ ትዕዛዛት፣ ጌታ በሰጣቸው የመንትያ የፍቅር ትዕዛዛት ሥር ይጠቀለላሉ።

ከአስርቱ ሕግጋት የመጀመሪያዎቹ ሶስቱን ትእዛዛት እናስታውስ። ትእዛዞቹ ምንድን ናቸው? እግዚአብሔርን ብቻ አምልኩ ለእርሱም ተገዙ፣ የአምላክን ስም በከንቱ አትጥሩ፣ ሰንበትን ቀድሱት። እግዚአብሔርን የሚወድ እኚህን ትእዛዞች ለመፈጸም አይቸገርም። ከእግዚአብሔር ውጭ ሌላ አያመልክም፣ የእግዚአብሔርንም ስም ያከብራል እንጂ በከንቱ አይጠራም፣ በሰንበትም በእግዚአብሔር እና በእጆቹ ሥራ ለመደነቅም ያርፋል።

የቀሩት ሰባቱ የሙሴ ትእዛዛት ወላጆች እንዲከበሩ፣ ዝሙት እንዳይፈጸም፣ ክቡሩ ሰው እንዳይገደል፣ ማንም እንዳይሰረቅ፣ በሐሰት ማንም እንዳይመሰክር፣ ማንም የባልንጀራን ቤትና ንብረት እንዳይመኝ ይከለክላሉ። ሁሉም ባልንጀራን ከመውደድ ጋር ይያዛሉ። ባልንጀራውን ወዶ እነዚህን የሚያደርግ የለም! ለባልንጀራው ያለውን ፍቅር ሳይጥል እኚህን ክልከላዎች ሰው መጣስ አይችልም።

እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራ መውደድ ተያይዘው ይቆማሉ፣ ተያይዘውም ይወድቃሉ። እግዚአብሔርን መውደድ ባልንጀራን ለመውደድ መሠረት ነው፤ እግዚአብሔርን መውደዳችንም የሚፈተነው ባልንጀራችንን በመውደዳችን ነው። ይህንኑ እውነታ ከሐዋርያው ጳውሎስ የበለጠ የተረዳው የለም። ስለዚህም ባልንጀራን መውደድን ብቻ የሕግ ሁሉ ፍጻሜ ይለዋል (ገላቲያ 5፡14፣ ሮሜ 8፡10-13)። ትዕዛዛቱ ሁል ጊዜ አንዳቸው ሌላውን ታሳቢ ያደርጋሉ። ባልንጀራን መውደድ ጥሎ እግዚአብሔርን መውደድ የሚባል ነገር የለም! እግዚአብሔርን ሳይወዱም እግዚአብሔር ሰውን በሚወድበት ፍቅር ባልንጀራን መውደድ አይቻልም።

ባልንጀራችንን ስንወድ እንኳን ክፉ ልናደርግበት ክፋውን መስማት አንፈልግም። ፍቅር ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ያለንን ትስስር ሲገዛ፣ ራሳችንን ለማስቀደም የሚጥረውን ተፈጥሮዋዊ ስሌታችንን ልጓም እናበጅለታለን፤ ሌላውን በማሰብ መኖርም ትግልነቱ ያበቃና በትጋት ልንፈጽመው የምንጠባበቀው ናፍቆታችን ይሆናል።

በጌታ ትምህርት ባልንጀራን መውደድ ዋንኛ ነገር መሆኑን ተከታዮቹ መገንዘባቸውን የትምህርታቸውና የኑሮዋቸው ጤንነት ያሳያል። ባልንጀራን መውደድም መልእክቶቻቸው እና የሕይወት ቅኝቶቻቸው ነበሩ (ሮሜ 13፡9፣ ገላቲያ 5፡13፣ ያዕቆብ 2፡8)። እኒህን የፍቅር ሕግጋት የሚያራክስ ክርስትና ክርስቶስን የሚከተል አይደለም!

ቪክተር ፓል ፈርኒሽ የተባለ የአዲስ ኪዳን ምሁር የእግዚአብሔር ፍቅር ለቤተ ክርስቲያን ምን ማለት እንደ ሆነ በጥሩ ቃላት ነግሮናል። "የእግዚአብሔር ፍቅር የክርስቶስ አካል ሕይወት ነው። ስለዚህም በክርስቶስ የአካል ብልቶች መካከል ፍቅር መዘዋወሩን ሲያቆም፣ የክርስቶስ አካል ያድፋል"[5] ብሏል። ቤተ ክርስቲያን ፍቅሯ ሲቀዘዝ፣ በአመጽ ትገናለች፤ ቅድስናም አይኖራትም (ማቴዎስ 24፡13)።

እንደ ክርስቶስ አካሎች ፍቅር ከሕይወታችን ሲጠፋ፣ ከቅድስና ሕይወታችን ይጎድላል። ቤተ ክርስቲያን ፍቅሯን ስትጥል አደጋ ውስጥ ትገባለች (ራዕይ 2፡4)። ከፍቅር ትእዛዛት ቤተ ክርስቲያን ስትጎድል የአገልጋይነት ጥሪዋን መኖር አትችልም፤ ከሌሎች ጋር ተዳብላ ተጨማሪ ሸክም ትሆናለች።

ቅዱሱ አውግስጢኖስ "መጽሐፍ ቅዱስን ሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት መካከል የተወሰኑትን በከፊል ተረድቻለው የሚል፣ መረዳቱን ግን እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን መውደድ በሚሉት መንትያ ትእዛዞች ላይ ያልገነባ፣ ቅዱሳት መጽሐፉቱን የመረዳት ነገር አልተሳካለትም"[6] ብሏል። መልእክታችንና ኑሮዋችን ባልንጀራን መውደድና እግዚአብሔርን መውደድ ሳያሳዩ፣ መጽሐፍ ቅዱሳችን ገብቶናል ብንል ራሳችንን እናታልላን፤ እውነትም በእኛ ዘንድ የለም።

## ይወደናል

ቅዱሳት መጽሐፍት የአምላካችንን የማይነጥፍ ፍቅሩ ይተርካሉ። ስለዚህም እነዚህን ቅዱሳት መጽሐፍት የፍቅር መጽሐፍት እንላቸዋለን። በቅዱሳት መጽሐፍት ታሪኮችና ትምህርቶች እግዚአብሔር ለሴቶች፣ ለወንዶች፣ ለህጻናት፣ ለታላላቆች፣ ለአይሁድ፣ ለአሕዛብ፣ ለቅዱሳንና ለኀጥአን ያለ ልዩነት ያሳየው ፍቅር በግልጽ ታይቷል። የቅዱሳት መጽሐፍት አምላካዊው መልእክት ሲጨመቅ "እወዳችኋለሁ" ይሆናል።

ስለ እግዚአብሔር ማለት የምንችለው "እግዚአብሔር ይወደናል" ብቻ ሳይሆን "እግዚአብሔር ፍቅር ነው" ጭምር ነው (1ኛ ዮሐንስ 4:8፣ 4፡16)። ፍቅር የእግዚአብሔር ማንነቱ ነው። ከእርሱስ ፍቅር ማን ሊለየን ይችላል (ሮሜ 8፡24-39)? ሌሎችን

5 Victor Paul Furnish, *Jesus according to Paul* (Cambridge: Cambridge University Press, 1993), 90.

6 Mark Vessey (ed.), *A Companion to Augustine* (Wiley-Blackwell, 2012), 206.

የመውደዳችን መደላደያውም እግዚአብሔር እኛን መውደዱን ማወቃችን ነው (1ኛ ዮሐንስ 4፡19)። እንደተወደደ የሚያውቅ መውደድ አይቸገርም።

ፍቅር የእግዚአብሔር ማንነቱ መሆኑን በብዙ መንገድ እናውቃለን። በስላሴ አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት ብናስብ መገለጫው ፍቅር ነው (ማቴዎስ 3፡17፣ ዮሐንስ 3፡35፣ 10፡17፣ 17፡24)። ፍቅር የኅብረት ሕይወት እንደመሆኑ በስላሴ አካላት መካከል ሁሌም ፍቅር አለ ማለት እንችላለን። የእግዚአብሔር ፍቅር ምንጭም ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው (ሮሜ 5፡50፤ 15፡30፤ ገላቲያ 5፡22-23)። እኛም ሌሎችን የምንወድበት ፍቅር ምንጩ ይኸው አምላካዊ ፍቅር እንጂ ሌላ አይደለም (ዮሐንስ 13፡34-35)።

በቅዱሳት መጽሐፍት ያየነው የእግዚአብሔር ፍቅሩ ይገርማል! “እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና” (ዮሐንስ 3፡16)። እግዚአብሔር ዓለሙን የወደደው ያለ አንዳች ምክንያት ሲሆን፣ ፍቅሩም አንድያ ልጁን በመሥዋዕትነት እንዲሰጥ አድርጎታል። ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ከመስጠት የሚበልጥ ፍቅር ደግሞ ለማንም የለም (ዮሐንስ 15፡13)!፡

እግዚአብሔር ማንነቱ ፍቅር ስለሆነ እኛን ለመውደድ ምክንያት አይፈልግም፤ ፍቅር የሆነ እርሱ የፍቅር እጥረት የለበትም! እርሱ ያለ አንዳች ምክንያት እንደወደደን ማወቅ ፍቅሩን እንድንቀበል ይረዳናል። በእግዚአብሔር ለመወደድ መሆን ያለብን ሌላ ነገር የለም፣ እግዚአብሔር ባለንበት ይቀበለናል፣ ተቀብሎንም ሳይፈርድብን ወደሚፈልገው ሕይወታችንን ይቀይረዋል። ስለዚህም፣ ማንም እንሁን ምንም በድፍረት እግዚአብሔር ይወደናል ማለት እንችላለን፤ ሁላችንም በፊቱ ውዶችና ክቡራን ነን! ከዚህም የተነሳ፣ እግዚአብሔር አይወድህም የሚል ድምጽ አጋንታዊ እንጂ አምላካዊ ድምጽ አለመሆኑንም በእርግጠኝነት እናውቃለን። እርሱ ይወደናል!

ፍቅሩን ለመረዳት፣ ፍጥረታችንን ላፍታ እናስብ። ለምን ፈጠረን? ለምን ዋጀን? ለምንስ በመግቦቱ ይመራናል? ለእግዚአብሔር ህላዌ ማናችንም አናስፈልግም፣ እርሱ ብቻውን ያለማናችንም ድጋፍ መኖር ይችላል፤ ከፍጥረት ሁሉ በፊት ነበርም። እርሱ ፍጥረት በሌለበት አንዳች ጎድሎት አልተቸገረም። “እርሱ ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎለው በሰው እጅ አይገለገልም።” አንዳች የማይፈልግ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረው ከፍቅር የተነሳ እንጂ ሌላ ምን ምክንያት ይኖረዋል!

እግዚአብሔር ፍጥረት ድንገት አልተከሰተበትም፣ ፈቅዶ አመጣው እንጂ። ስለዚህም፣ ፍቅር ፍጥረትን ያስገኘና ደግፎ አሁንም ድረስ የሚያኖር አምላካዊ ነጻ ፈቃድ ነው። ድነታችንንም እንዲሁ እናስብ። ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን ሞትን የቀመሰው ፍቅር ግድ ብሎት ነው። እርሱ ቢሻ ሁሉን ደምስሶ ከአዲስ መጀመር ይችል ነበር፤ ፍቅር መሆኑ

ግን ከእኛ አንዱ እንዲሆን አደረገው። ይህንን የተገነዘበው ስኮት ጄ ጆንስ "እግዚአብሔር የሚፈጥረው፣ የሚዋጀውና ዓለምን የሚያድነው ፍቅር ስለ ሆነ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ይወዳል።" ብሏል።[7]

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን ፍቅር የገለጸበት የአባትነት ምሳሌ ልብን ይነካል። ነቢዩ ሆሴህ በምዕራፍ 11፡1-4 ላይ የእግዚአብሔርን ፍቅር የተረከው "እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድሁት፥ ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት።...እኔም ኤፍሬምን ክንዱን ይዤ በእግሩ እንዲሄድ መራሁት፤ እኔም እፈውሳቸው እንደ ነበርሁ አላወቁም። በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው፤ ለእነርሱም ቀምበርን ከጫንቃቸው ላይ እንደሚያነሣ ሆንሁ፥ ድርቆሽም ጣልሁላቸው።" ሲል ነው።

እግዚአብሔር እስራኤልን የወደደበት መንገድና እስራኤል ለፍቅሩ የሰጠው ምላሽ ይገርማል። እግዚአብሔር ልጆቹን ከባርነት እስራት ፈርቶ አወጣቸው፤ እስራኤል ግን አላመሰገነም። እስራኤል በወደዳቸው በእርሱ ላይ አመጹ፣ ሌሎች አማልክትን ለማምለክም ፊታቸውን ከእርሱ ዘወር አደረጉ። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳናዊ ፍቅር ግን ከእነርሱ ጋር ጸና (ኤርሚያስ 31፡3)። እርሱ ለእኛ ያለው ፍቅር እናት ለልጇ ካላት ፍቅርም ይልቅ ይጠልቃል (ኢሳይያስ 49፡15፣ 66፡13)።

የእግዚአብሔርን ፍቅር የማይነጥፍና ተንከባካቢ መሆኑንም የጌታችን ምሳሌዎች ያሳዩናል። ሉቃስ 15ን እንደ ምሳሌ እናንሳ። ፍቅር ከመቶዎቹ በጎች ውስጥ የጠፋውን አንዱን በግ፣ ከአስር ድሪም መካከል የጠፋውን አንድን ድሪም ፈልጓል፤ የጠፋውንም ልጅ ተቀብሏል። ምሳሌዎቹ እስኪያገኘን ድረስ የማያንቀላፋውን እግዚአብሔርን ለሁላችን ያለውን የማያልቅ ፍቅር ያሳያሉ። እግዚአብሔር በእርግጥም ይወደናል። መጠርጠር ካለብን መጠርጠር ያለብን እኛ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ያለንን የጠበበ ግንዛቤ እንጂ እርሱ ስለ እኛ ያለውን ፍቅር አይደለም!

በነዚህ ሁሉ ምስክሮች ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር መራጭ እንደሆነ የሚያስቡ አይጠፉም። ይህ አስተሳሰብ ልክ አይደለም። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 5፡8 ላይ "...ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።" (ሮሜ 5፡8) በማለት የፍቅሩን አካታችነት ገልጾልናል። ክርስትያኖችም ለዓለም ያለን መልእክት እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ለወደዳችሁ ጌታ የፍቅር ምላሽን ስጡ የሚል ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ፣ ለውጥ የሌለበት እና ሁሉን አካታች ስለሆነ ማንም ከእርሱ ፍቅር ውጭ አይደለም።

---

7 Jones, *The Evangelistic Love of God and Neighbor*, 33.

ፍቅር የእግዚአብሔር የማንነቱ መገለጫ እንደመሆኑ፣ ከፍቅር ውጭ እግዚአብሔርን ልናስበው አይቻልም፤ አይገባምም። ዮሐንስ “ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።” በማለቱ ሁለት ነገሮች እንገነዘባለን። አንደኛው፣ ፍቅር የእግዚአብሔር ማንነቱ መሆኑን ሲሆን ሁለተኛው ያለ ፍቅር እግዚአብሔርን እናውቃለን ማለት አለመቻሉን ነው። ለአምላካችን ፍቅር የሆነ ጊዜ የሚተገብረው ሲያሻው የሚተወው አይደለም። ከፍቅር ውጭ እግዚአብሔር ሊታወቅ አይችልም።

ለእግዚአብሔር ፍቅር ምላሽስ ምን ሊሆን ይገባል? ለአምላካዊ ፍቅር ምላሻችን እርሱን እና ባልንጀራንም መውደድ ነው። የወደደን አምላክ በወደደን ፍቅሩ ሁሉን እንድንወድ ይጠብቅብናል። ያለምንም ቅድመ ሁኔታ፣ በቸርነቱና ልጁን መሥዋዕት አድርጎ እንደ ወደደን ሁሉ፣ እኛም ያለቅድመ ሁኔታ፣ በቸርነትና በመሥዋዕትነት እንድንወድ ተጠርተናል። ከቅድስና ባሕርዩ እንደተካፈልን ልጆቹ፣ ያለ ልዩነት ሁሉን መውደድ ጥሪያችን ነው። ጥሪያችን የፍቅር አምባሳደርነት ሲሆን፣ የፍቅር ንግግርና ከፍቅር የሚመነጭ አገልግሎት ኑሮዋችን ሊሆን ይገባል።

እግዚአብሔር እንደወደደን ያወቅነው ሥራውን ተመልክተን እንደሆነ ሁሉ፣ እኛም ፍቅርን ለሰዎች የምናሳይበት በርካታ እድሎች አሉን። ሰዎች በምናደርግላቸው እንክብካቤ ውስጥ ፍቅራችንን ያያሉ። በሕይወታቸው ለሚውተረተሩ፣ ለሚታገሉ የምናሳየው ርህራሄ ፍቅራችንን ይገልጣል። በንግግራችን ሌሎችን ለማነጽ ስንተጋ፣ ለሌሎች ስሜት ስንጠነቀቅ፣ ሰዎችን ስናበረታታ፣ ለበጎ ነገሮቻቸው እውቅናን ስንሰጥ ፍቅራችንን ገልጸናል። በአንጻሩ ሰዎችን ስንበድል፣ ስናሰቃይ፣ ክፉ ስንሆንባቸው፣ እውነትን መነጋር ሲያቅተን፣ በብሔር፣ በዘር፣ በሐይማኖት፣ በመደብ ላይ ተመስርተን ክፍፍልን ስናደርግ ደግሞ ፍቅርን ነፍገናል።

## እንወደዋለን?

ጌታችን ሞትን ድል ከነሳ በኋላ፣ ጴጥሮስን ፈታኝ ጥያቄ ጠየቀው። ጥያቄውንም ሶስቴ ደጋገመው። ጥያቄው “ትወደኛለህ?” የሚል ነበር (ዮሐንስ 21፡ 14-17)። ይህንን ጥያቄ እግዚአብሔርም ዛሬም እያንዳንዳችንን እንደሚጠይቀን አስባለሁኝ። መልሳችሁን ምን ይሆን? እግዚአብሔርስ መልሳችንን እንዴት ይመዝነዋል?

የጌታንና የጴጥሮስን ምልልስ ልብ ካልን አንድ ነገር ፍንትው ይልልናል። ጴጥሮስ መልሱ “አንተ ታውቃለህ” ነበር። ጌታም የአንተ ተውቃለህ መልሱን ተከትሎ ሌሎችን የማገልገል ኃላፊነትን ሰጥቶቷል። ኃላፊነቱ የመጠበቅና የማሰማራት ነበር። ከጌታችን መልስ እግዚአብሔርን መውደድ ሌሎችን ከመንከባከብ ፈጽሞ ሊነጠል እንደማይቻል አውቀናል። ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር ሥጋን የሚለብሰው ለሌሎች በምናሳየው ተግባር በኩል ነው።

ጌታ ይህንኑ እውነታን ከትንሣኤ በፊትም ለደቀ መዛሙርቱ በግልጽ ቋንቋ ነግሯቸዋል። "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ።" (ዮሐንስ 14፡15-16) በማለት፤ የፍቅር መፈተኛው ትእዛዙን መጠበቅ መሆኑን ተናግሯል። እግዚአብሔርን የመውደዳችን መገለጫው በእርሱ መንገድ ለመሄድ መናፈቅና ትእዛዙን በሙሉ ልብ መቀበል መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ስለዚህም የትወደኛለህ ጥያቄ በውስጠ ታዋቂነት ታሳቢ ያደረገው ነገር፣ ዋጋ በሚያስከፍለው በትእዛዙ መንገድ ለመጓዝ ተዘጋጅታችኃል ወይ የሚል ነው።

ጌታም ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው አዲሱ ትእዛዝ እርስ በእርሳቸው እንዲዋደዱ እንጂ ሌላ አይደለም (ዮሐንስ 13፡34፣ 15፡12-13)። የእርስ በእርስ ፍቅር መገለጫው ደግሞ አንዳችን ሌላችን ማገልገላች ነው። ስለዚህም፣ ስንወድ ሕይወታችን መሥዋዕትነት ያለበት ማካፈል ይኖረዋል። እግዚአብሔርን መውደድና ማወቅ፣ ሌሎችን ከመውደድ ጋር መቆራኘቱ ሹክ የሚለን ነገር አለ። ሌሎችን አለመውደድ በእርሱ መልክ የተፈጠሩትን አለመውደድ ስለሆነ የእግዚአብሔርን መልክ አለመውደድ ይሆናል።

አንዳንዶቻችን ሌሎችን የመውደድ ዋንኛ መገለጫው በውስጣችን ሌሎችን አስመልክቶ የሚሰማን ነገር ይመስለናል። አውነታው ግን የፍቅር መገለጫው በርካታ ቃላትን እየከሸኑ መደርደር ሳይሆን ድርጊት ነው። የፍቅራችን ምስክሩ ሆነ መፈተኛው ድርጊታችን እንጂ ንግግራችን አይደለም። ፍቅር ስሜት ብቻ ቢሆን ኖሮ ውደዱ ተብለን አንታዘዝም ነበር። ማንም ስሜትን በትእዛዝ በሌላው ሰው ውስጥ መፍጠር ስለማይችል፣ ውደዱ ማለት ትርጉም ባልኖረው ነበር።

መውደድ ትእዛዝ መሆኑ በኃይሉ ድንገት ተገፍተን የምንወድቅበት እቅፍ አለመሆኑን ያስገነዝበናል። ሌላውን መውደድ አዕምሮዋችንንም የምናሰለጥንለት ምግባርም መሆኑን ያስታውሰናል። ፍቅራችን ከመረዳታችን ይወለዳል፣ በመረዳታችንም ይበለጽጋል።

እግዚአብሔርን መውደድ ባልንጀራን ከመውደድ ጋር ሊፋታ አለመቻሉን ከማቴዎስ 25፡31-46ን እንመልከት። በዚህ ክፍል ጌታችን በክብር ሊፈርድ ሲመጣ የሚሆነው እናገኛለን። ሕዝቦች ሁሉ ፍጻሜያቸውን ሊሰሙ በፊቱ ይሰበሰባሉ። ፍርዱ ከፊሉን በቀኝ ለዘላለማዊ ሕይወት፣ በስተግራ ደግሞ ለዘላለማዊ ፍርድ ይለያል። የውዳሴውና የኩነኔው ሚዛን ምን ነበር? መልሱ ጌታ ተርቦ፣ ተጠምቶ፣ እንግዳ ሆኖ፣ ታርዞ፣ ታሞ፣ እና ታስሮ ምን አደረግንለት በሚለው ላይ ተመስርቷል።

ጌታ እንዳበላነው፣ እንዳጠጣነው፣ በእንግድነት ተቀብለን እንዳስተናገድነው፣ ታርዞ እንዳለበስነው፣ ታሞ እንደጠየቅነው፣ ታስሮ ወደ እርሱ እንደመጣን የሚቆጥረው እኒህን አገዛዎችን ከእኛ ለሚፈልጉ ለታናናሾች ስናደርግ ነው። የጌታ መልእክት "እግዚአብሔርን መውደዳችን ባልንጀራችን ከመውደዳችን ተነጥሎ አይታይም!" ነው።

ፍቅር በዋነኛነት ንግግር ሳይሆን ድርጊት ነው ስንል፣ ተግባራችን የመነጨበት ልብ በአምላክ አይመዘንም ማለት ግን አይደለም። እግዚአብሔር ልብን ይመረምራል (ኤርሚያስ 17፡10፤ መዝሙር 44፡21)። ድርጊታችን የፍቅር መገለጫው እንደ ሆነው ሁሉ፣ ከፍቅር የተፋታ ድርጊትም እንዲሁ ከንቱ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህንኑ በመገንዘብ ያለንን ሁሉ ብንሰጥ ፍቅር ግን ከሌለን ከንቱ መሆኑን ነግሮናል። ይኸም የሚያሳየን መልካም ተግባር ከፍቅር ውጭ ሊፈጸም የመቻሉን እውነታ ነው። ክርስትናም ፍቅርን ይሰብካል፣ ከንግግር በበለጠ ድርጊትን ያስቀድማል፣ ድርጊትንም ከመልካም ልብ ጋር አብሮ ይገምደዋል (1ኛ ቆሮንቶስ 13)።

## ንድፍ

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ምንድን ነው? እግዚአብሔርን የመውደድ ተግባራዊ ምልክቱ ባልንጀራን መውደድ መሆኑን ማመልከትና እኛንም የባልንጀራን መውደድ አምባሳደር እንድንሆን መቀስቀስ ግቡ ነው። ይህን ለማድረግም የብሉይ ኪዳንን እና የአዲስ ኪዳንን ቅዱሳት መጽሐፍትን ልክ እንደ ልባሞቹ የቤሪያ ሰዎች ከምዕራፍ ሶስት እስከ ምዕራፍ አራት እንመረምራለን። በምዕራፍ አምስትም፣ ባልንጀራን መውደድን በምን በመልኩ በተዕለት ተዕለት ኑሮዋችን ውስጥ እንተገብረዋለን የሚለውን እናነሳለን። በመደምደሚያው ምዕራፍም ሁላችንም የባልንጀራን መውደድ አምባሳደሮች በመሆን ፍቅር ለተጠማው ዓለም የፍቅር መልእክት እንድናቀርብ እና ለከበቡን ችግሮች መፍትሄ እንድንሆን እንጋብዛለን።